# ጥራቱን የጠበቀ ማር አመራረት፣ አያያዝ እና ግብይት

ንቦች ለልማት በኢትዮጵያ
BfdE
Bees for development Ethiopia

## የማር የሚቆረጥበትን ወቅት ማወቅ

ማር መድረሱን የምናውቅባቸው ምልክቶች፤

- ማር ማር መሽተት፣
- ንቦች በዓይነብልጡ ላይ ተከማችተው ይታያሉ፣
- ድንጉላ ንቦች በብዛት በቀፎው ስር ሞተው ይገኛሉ።

ማር እንደ አካባቢው ሁኔታ በአብዛኛው ከጥቅምት እስከ ታህሳስ ወይም ከግንቦት እስከ ሰኔ ባሉት ወራቶች ሊቆረጥ ይችላል



## ከባህላዊ እና ከሽግግር ቀፎ የተመረተን ማር ማጣራት

- የበሰለውን ማር በየቀለሙ መለየት፣
- ከባህላዊ እና ከሽግግር ቀፎ የተገኙትን ማር እንደተቆረጠ ወዲያዉኑ መፈትፈት፣
- የተፈተፈተውን ማር በንጹህ ባልዲ ማድረግ እና ለ12 ሰዓት ማቆየት፣ ሰፈፉን በማንኪያ ማንሳት ወለላውን ማር በጨርቅ፣ በወንፊት ማጣራት
- በጠርሙስ ማሸግ





## ማር ለመቁረጥ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት

ማርን በንቦች ሳይነደፉ ተረጋግቶ ለመቁረጥ ሙሉ ትጥቅ (ዓይነ እርግብ፣ ቱታ፣ የእጅ ጓንት፣ ቦት ጫማ) ያስፈልጋሉ፤

በተጨማሪም ማጨሻ፣መር፣ሙሬ/ብሩሽ፣ ቢላዋ፣ ባትሪ፣ የማር መያዣ ዕቃ ያስፈልጋሉ



## ከዘመናዊ ቀፎ የተመረተን ማር ማጣራት

- የበሰለሰውን የማር እንጀራ ከነፍሬሙ ማውጣት
- በንቦች የታሸገውን የማር እንጀራውን በዓይነበጎ መግለጫ ቢላዋ መክፈት
- ዓይነበጎው የተከፈተውን የማር እንጀራ በማጣሪያ ማሽን ውስጥ በማስገባት ማጣራትና ወለላውን መለየት
- ወለላውን ማር በወንፊት ወይም በደበላ ጨርቅ በማጣራት በብርጭቆ ማሸግ
- ወለላው የወጣለትን የማር እንጀራ መልሶ ቀፎው ውስጥ በማስገባት ንቦች በድጋሚ ማር እንዲሠሩበት ማድረግ







## ማር የሚቆረጥበትን ቀፎ መክፈት

ሽታ አልባ ጭስ (የበቆሎ ቀረቀንዳ፣ የገብስ ወይም የስንዴ ገለባ፣ ጭድ፣ የኬሻ ቃጫ) በትንሹ ካጨሱ በኋላ ቀፎውን መክፈት

ማሳሰቢያ
የከብት ኩበት እና የጋማ ከብት ፋንድያ መጠቀም የማርን ጥራት በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳዋል






## የማር አቀማመጥ

- ማሩን ለማስቀመጥ ንፋስ በማያስገባ እና ክዳን ባለው ጎማ ወይም ጠርሙስ አድርጎ በንፁህ ቀዝቃዛ እና ደረቅ ቦታ ማስቀመጥ ያስፈልጋል
- ማር ወዲውኑ እንደተመረተ ለገበያ ማቅረቡ ይመረጣል



## የበሰለ እና ያልበሰለ ማር መለየት እና መቁረጥ

- ማር በሚቆረጥበት ጊዜ የበሰለ (በንቦች የታሸገ) እና ያልበሰለውን ማር በመለየት በተለያየ እቃ ማስቀመጥ፣
- ያልበሰለ ማር በቀላሉ ስለሚበላሽ ለምግብነት ማዋል ወይም ወዲያውን ለገበያ ማቅረብ፣
- የበሰለ እና ያልበሰለ ማር መቀላቀል ወይም አብሮ መታሸት የለበትም፣
- ከእጭ እና ከድኝ ጋር የተቀላቀለ ማርን ለንቦች ቀለብ እንዲሆን መተው ተገቢ ነው።




## ማርን ለገበያ ማቅረብ

- የተቆረጠውን ማር ወዲያውኑ ለገበያ ማቅረብ ያስፈልጋል
- ማር ለገበያ ሲቀርብ በሚከተሉት ቁሳቁሶች መቅረብ ተገቢ ነዉ፣
- በፕላስቲክ እቃዎች
- በማይዝጉ እቃዎች
- ማርን ለገበያ የሚቀርብበት መንገዶች
- እንጀራ ማር
- የተጣር ማር
- እንጀራ እና የተጣራ ማር ተቀላቅሎ
- ክሬምድ ማር




ይህ ጥራቱን የጠበቀ ማር አመራረት፣ አያያዝ እና ግብይት በሚል የተዘጋጀው ፖስተር በንብ ሃብት ዘርፍ የስልጠና እና የምክር አገልግሎት በሚሰጠው ንቦች ለልማት ኢትዮጵያ በሚባል ድርጅት ነው። የንብ ማነብ ሥራ ተፈጥሮ ሃብትን ለመጠበቅ፣ የሥራ እድልን ለመፍጠር እና ደኅነትን ለመቅረፍ እንደሚረዳ ንቦች ለልማት በኢትዮጵያ ያምናል።

UKaid
from the British people



ንቦች ለልማት ኢትዮጵያ
ፖ.ሣ.ቁ.786
ሞባይል: 0918761182
ኢ-ሜይል: tilahun_gebey@yahoo.com
ባህር ዳር